የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

**OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

ሃያ ስድስተኛ ዓመት ቁጥር ፷፮
አዲስ አበባ ሐምሌ ፲፬ ቀን ፪ሺ፲፪ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

26th Year No.66
ADDIS ABABA 21st July, 2020

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፲፪/፪ሺ፲፪ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በኳታር መንግስታት መካከል የተፈረመው የኢንቨስትመንት ማስፋፋት እና ጥበቃ ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ............................ገጽ ፲፪ሺ፮፻፹፯

## Content

Proclamation No.1212/2020

The Agreement between the Governments of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the State of Qatar on the Promotion and Reciprocal Protection of Investment Ratification Proclamation ……………………………......................Page 12,687

### አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፲፪/፪ሺ፲፪

### በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በኳታር መንግስት መካከል የተፈረመውን የኢንቨስትመንት ማስፋፋት እና ጥበቃ ስምምነት ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በኳታር መንግስታት መካከል የኢንቨስትመንት ማስፋፋት እና ጥበቃ ስምምነት ኅዳር ፭ ቀን ፪ሺ፲ ዓ.ም. በዶሃ ኳታር የተፈረመ በመሆኑ፤

ይህንኑ ስምምነት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሰኔ ፲፰ ቀን ፪ሺ፲፪ ዓ.ም ባካሄደው መደበኛ ስብሰባው ያፀደቀው በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ ፶፭ (፩) እና (፲፪) መሰረት የሚከተለው ታውጇል::

### PROCLAMATION NO.1212/2020

### A PROCLAMATION TO RATIFY THE AGREEMENT BETWEEN THE GOVERNMENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE GOVERNMENT OF THE STATE OF QATAR ON THE PROMOTION AND RECIPROCAL PROTECTION OF INVESTMENT

**WHEREAS**, the Agreement between the Governments of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the State of Qatar on the Promotion and Reciprocal Protection of Investment was signed in Doha Qatar on 14th November, 2017.

WHEREAS, the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified the said Agreement at its session held on 25th day of June, 2020;

**NOW, THEREFORE**, in accordance with Article 55 (1) and (12) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows.

፩. **<u>አጭር ርዕስ</u>**

ይህ አዋጅ "በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በኳታር መንግስታት መካከል የተፈረመው የኢንቨስትመንት ማስፋፋት እና ጥበቃ ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፲፪/፪ሺ፲፪."ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል::

፪. **<u>ስምምነቱ ስለመፅደቁ</u>**

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በኳታር መንግስታት መካከል ኅዳር ፭ ቀን ፪ሺ፲ ዓ.ም. በዶሃ ኳታር የተፈረመው የኢንቨስትመንት ማስፋፊያ እና ጥበቃ ስምምነት ፀድቋል::

፫. **<u>አስፈፃሚ አካል</u>**

የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን ስምምነቱን የማስፈፀም ኃላፊነት በዚህ አዋጅ ተሰጥቶታል::

፬. **<u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>**

ይህ አዋጅ በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል::

**አዲስ አበባ ሐምሌ ፲፬ ቀን ፪ሺ፲፪ ዓ.ም**

**ሣህለ ወርቅ ዘውዴ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

1. **<u>Short Title</u>**

This Proclamation may be cited as "the Agreement between the Governments of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the State of Qatar on the Promotion and Reciprocal Protection of Investment Ratification Proclamation No.1212/2012".

2. **<u>Ratification of the Agreement</u>**

The Agreement between the Governments of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the State of Qatar on the Promotion and Reciprocal Protection of Investment signed in Doha Qatar on 14th November, 2017, is hereby ratified.

3. **<u>Implementing Organ</u>**

The Ethiopian Investment Commission is hereby empowered to implement the Agreement.

4. **<u>Effective Date</u>**

This Proclamation shall come into force upon publication in the *Federal Negarit Gazette*.

**Done at Addis Ababa on this 21st day of July, 2020.**

**SAHELE-WORK ZEWDE**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**